# ሁለት ኪሩቤል
# ከተቀጠቀጠ ወርቅ ሥራ



- ዘጸ.20:23፤ በአጠገቤ ምንም አታድርጉ፤ የብር አማልክት የወርቅም አማልክት ለእናንተ አታድርጉ።

- ምሳ.28:9 ሕግን ከመስማት ጆሮውን የሚመልስ ጸሎቱ አስጸያፊ ናት።

- ዕን.2:18፤ የተቀረጸውን ምስል ሠሪው የቀረጸው ለምን ጥቅም ነው? ዲዳንም ጣዖት ይሠራ ዘንድ ሠሪው የታመነበቱ፥ ሐሰትን የሚያስተምር ቀልጦ የተሠራ ምን ይጠቅማል? 19 እንጨቱን ንቃ፥ ዲዳውንም ድንጋይ ተነሣ ለሚለው ወዮለት! በውኑ ይህ ያስተምራልን? እነሆ፥ በወርቅና በብር ተለብጦአል፥ ምንም እስትንፋስ የለበትም። 20 እግዚአብሔር ግን በተቀደሰ መቅደሱ አለ፤ ምድርም ሁሉ በፊቱ ዝም ትበል።

# ዘጸ.25:17-20፤ ዘጸ.37:7-9

- 17 ከጥሩ ወርቅም ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፥ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል የሆነ የስርየት መከደኛ ሥራ። 18 ሁለት ኪሩቤል ከተቀጠቀጠ ወርቅ ሥራ (ዕብ.-አሳህ)፥ በስርየት መከደኛውም ላይ በሁለት ወገን ታደርጋቸዋለህ። 19 ከስርየት መከደኛውም ጋር አንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን፥ ሁለተኛውንም ኪሩብ በሌላው ወገን አድርገህ በአንድ ላይ ትሠራዋለህ። 20 ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ወደ ላይ ይዘረጋሉ፥ የስርየት መከደኛውንም በክንፎቻቸው ይሸፍናሉ፥ ፊታቸውም እርስ በርሱ ይተያያል፤ የኪሩቤልም ፊቶቻቸው ወደ ስርየት መከደኛው ይመለከታሉ።
- 7 ሁለት ኪሩቤልንም ከተቀጠቀጠ ወርቅ ሠራ፤ በስርየት መከደኛውም ላይ በሁለት ወገን አደረጋቸው። 8 ከስርየት መከደኛውም ጋር አንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን፥ ሁለተኛውንም ኪሩብ በሌላው ወገን አድርጎ በአንድ ላይ ሠራቸው። 9 ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ወደ ላይ የዘረጉ ሆኑ፥ የስርየት መከደኛውንም በክንፎቻቸው ሸፈኑ፥ እርስ በርሳቸውም ተያዩ፤ የኪሩቤልም ፊቶቻቸው ወደ መከደኛው ተመለከቱ።



# ዘጸአት 25፡21-22

- 21 የስርየት መክደኛውንም በታቦቱ ላይ ታደርገዋለህ፤ እኔም የምሰጥህን ምስክር በታቦቱ ውስጥ ታኖረዋለህ። 22 በዚያም ከአንተ ጋር እገናኛለሁ፤ የእስራኤልንም ልጆች ታዝዝ ዘንድ የምሰጥህን ነገር ሁሉ፥ በምስክሩ ታቦት ላይ ባለው **በሁለት ኪሩቤል መካከል፥ በስርየት መክደኛውም ላይ ሆኜ እነጋገርሃለሁ**።



# 1ነገ.6:23-27

- በቅድስተ ቅዱሳኑም ውስጥ ቁመታቸው አሥር ክንድ የሆነ ከወይራ እንጨት ሁለት ኪሩቤል ሠራ። 24 የኪሩብም አንደኛው ክንፍ አምስት ክንድ፥ የኪሩብም ሁለተኛው ክንፍ አምስት ክንድ ነበረ፤ ከአንደኛው ክንፍ ጫፍ ጀምሮ እስከ ሁለተኛው ክንፍ ጫፍ ድረስ አሥር ክንድ ነበረ። 25 ሁለተኛውም ኪሩብ አሥር ክንድ ነበረ፤ ሁለቱም ኪሩቤል አንድ ልክና አንድ መልክ ነበረ። 26 የአንዱ ኪሩብ ቁመት አሥር ክንድ ነበረ፥ የሁለተኛውም ኪሩብ እንዲሁ ነበረ። 27 ኪሩቤልንም በውስጠኛው ቤት አኖራቸው፤ የኪሩቤልም ክንፎቻቸው ተዘርግተው ነበር፤ የአንዱም ኪሩብ ክንፍ አንደኛውን ግንብ ይነካ ነበር፥ የሁለተኛውም ኪሩብ ክንፍ ሁለተኛውን ግንብ ይነካ ነበር፤ የሁለቱም ክንፎች በቤቱ መካከል እርስ በርሳቸው ይነካኩ ነበር።

# 1ነገ.6:31-35

- ለቅድስተ ቅዱሳኑም መግቢያ ከወይራ እንጨት ደጆች ሠራ፤ መድረኩንና መቃኖቹን ደፉንም አምስት ማዕዘን አደረገ። 32 ሁለቱንም ደጆች ከወይራ እንጨት ሠራ፤ የኪሩቤልንና የዘንባባ ዛፍ የፈነዳም አበባ **ምስል**[1] **ቀረጸባቸው**[2] ፥ በወርቅም ለበጣቸው፤ ኪሩቤልናና የዘንባባውን ዛፍ በወርቅ ለበጣቸው። 33 እንዲሁም ለመቅደሱ መግቢያ ከወይራ እንጨት አራት ማዕዘን መቃን አደረገ። 34 ሁለቱንም ደጆች ከጥድ እንጨት ሠራ፤ አንዱ ደጅ በማጠፊያ ከተያያዘ ከሁለት ሳንቃ ተደረገ፥ ሁለተኛውም ደጅ በማጠፊያ ከተያያዘ ከሁለት ሳንቃ ተደረገ። 35 የኪሩቤልንና የዘንባባ ዛፍ የፈነዳም አበባ **ምስል ቀረጸባቸው፤** በተቀረጸውም ሥራ ላይ **በወርቅ ለበጣቸው።**

- 1. מִקְלַעַת(miqla`ath – carving) ሚክላህት -- ተቀርጾ የወጣ ቅርጽ ወይም እንደ ሐውልት አድርጎ መቅረጽ፤
- 2. קָלַע (qala` - carved) ካላህ -- ቀርጾ ወይም ፈልፍሎ ማውጣት

# 2ዜና.3:5-7፤ 11-12

- ታላቁንም ቤት በጥድ እንጨት ከደነው፥ በጥሩም ወርቅ ለበጠው፤ **የዘንባባና የሰንሰለት አምሳል ቀረጸበት**። 6 ቤቱንም በዕንቍ አስጌጠው፤ ወርቁንም የፈርዋይም ወርቅ ነበረ። 7 ቤቱንም ሰረገሎቹንም መድረኮቹንም ግንቦቹንም ደጆቹንም በወርቅ ለበጠ፤ **በግንቦቹም ላይ ኪሩቤልን ቀረጸ**[1]።
- 11 የኪሩቤልም ክንፎች ሀያ ክንድ ሙሉ ተዘርግተው ነበር፤ የአንዱ ኪሩብ ክንፍ አምስት ክንድ ነበረ፥ የቤቱንም ግንብ ይነካ ነበረ፤ ሁለተኛው ክንፍ አምስት ክንድ ነበረ፥ የሁለተኛውንም ኪሩብ ክንፍ ይነካ ነበር። 12 የሁለተኛውም ኪሩብ ክንፍ አምስት ክንድ ነበረ፥ የቤቱንም ግንብ ይነካ ነበር፤ ሁለተኛውም ክንፍ አምስት ክንድ ነበረ፥ የሌላውንም ኪሩብ ክንፍ ይነካ ነበር።

- 1- פָּתַח (pathach-graved) - ፓውታክ- እላዩ ላይ ፈልፍሎ መቅረጽ

# ዘዳ.4፡12-19

- እግዚአብሔርም በእሳት ውስጥ ሆኖ ተናገራችሁ፤ የቃልን ድምፅ ሰማችሁ፥ **መልክ ግን አላያችሁም፤** ድምፅን ብቻ ሰማችሁ። 13 ታደርጉትም ዘንድ ያዘዛችሁን ቃል ኪዳን አሥሩን ቃላት ነገራችሁ፤ በሁለቱም በድንጋይ ጽላቶች ላይ ጻፋቸው። 14 ትወርሱአት ዘንድ ተሻግራችሁ በምትገቡባት ምድር የምታደርጉአትን ሥርዓትና ፍርድ አስተምራችሁ ዘንድ እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ አዘዘኝ። 15 እግዚአብሔር በኮሬብ በእሳት ውስጥ ሆኖ በተናገራችሁ ጊዜ **መልክ ከቶ አላያችሁምና እጅግ ተጠንቀቁ፤** 16 እንዳትረክሱ፥ **የተቀረጸውን ምስል የማናቸውንም ነገር ምሳሌ፥ በወንድ ወይም በሴት መልክ የተሠራውን፥** 17 በምድር ላይ ያለውን የእንስሳን ሁሉ **ምሳሌ፥** በሰማይም በታች የሚበርረውን የወፍን ሁሉ **ምሳሌ፥** 18 በምድርም ላይ የሚሽከረከረውን ሁሉ **ምሳሌ፥** ከምድርም በታች በውኃ ውስጥ የሚኖረውን የዓሣን ሁሉ **ምሳሌ እንዳታደርጉ፥** 19 ዓይኖችህን ወደ ሰማይ አንሥተህ አምላክህ እግዚአብሔር ከሰማይ ሁሉ በታች ላሉት አሕዛብ ሁሉ የሰጣቸውን ፀሐይንና ጨረቃን ከዋክብትንና የሰማይን ሠራዊት ሁሉ ባየህ ጊዜ፥ ሰግደህላቸው አምልከሃቸውም እንዳትስት ተጠንቀቅ።

# የነሐሱ እባብ

- ዘኊ.21:8-9፤ ሙሴም ስለ ሕዝቡ ጸለየ። እግዚአብሔርም ሙሴን። እባብን ሥርተህ በዓላማ ላይ ስቀል፤ የተነደፈውም ሁሉ ሲያያት በሕይወት ይኖራል አለው። 9 ሙሴም የናሱን እባብ ሥርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ፤ እባብም የነደፈችው ሰው ሁሉ የናሱን እባብ ባየ ጊዜ ዳነ።
- 2ነገ.18:3-7፤ እርሱም አባቱ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ **በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገርን አደረገ**። በኮረብታም ያሉትን መስገጃዎች አስወገደ፥ ሐውልቶችንም ቀለጣጠመ፥ የማምለኪያ ዐፀዶቹንም ቈረጠ፤ የእስራኤልም ልጆች እስከዚህ ዘመን ድረስ ያጥኑለት ነበርና **ሙሴ የሠራውን የናሱን እባብ ሰባበረ**፤ ስሙንም ነሑሽታን ብሎ ጠራው። 5 በእስራኤልም አምላክ በእግዚአብሔር ታመነ፤ ከእርሱም በኋላ ከእርሱም በፊት ከነበሩት ከይሁዳ ነገሥታት ሁሉ እርሱን የሚመስል አልነበረም። 6 ከእግዚአብሔርም ጋር ተጣበቀ፥ እርሱንም ከመከተል አልራቀም፥ እግዚአብሔርም ለሙሴ ያዘዘውን ትእዛዛቱን ጠበቀ። 7 እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ፥ የሚሄድበትም መንገድ ተከናወነለት፤

# ምስለ ፍቁር ወልዳ ወይስ?

- ድንግል ማርያምና ሕጻኑ ኢየሱስ

  ወይስ
- ጥንታዊያን የባቢሎን አማልክት ?

# ጥንታዊ የባቢሎናውያን የውሸት አማልክት?



# ኒምሮድ፣ ሳሚራሚስና ታሙዝ

- ኒምሮድ (ዜዉስ)_- የፀሐይ አምላክ
- ሳሚራሚስ - የጨረቃ አምላክ

  - የኒምሮድ ሚስትና የታሙዝ እናት

  በግሪክ - የዜዉስ እህትና ሚስት/

  በሮም - የጁፒተር ሚስት/

  በተጨማሪም ሬ ወይም ኦፕስ የግሪክ ባለ ቀንድ አምላክ ክሮኖስ እህትና ሚስት


- ታሙዝ (ሆረስ)- ልጃቸው

# ሦስቱ በጥንት እንደ ሥላሴ ሲመለኩ

- አባት - ናምሩድ
- እናት - ሳሚራሚስ
- ልጅ - ታሙዝ

- ልዩ ምልክት ----›







Semiramis
Nimrod
Diosa Luna
de la Antigua
Babilonia
Tammuz
Dios-Sol
Esposa y
Madre de
Nimrod
Nacido 25 Dic








Sermiramis was initially included in the pagan Babylonian trinity as the holy spirit ( the dove) later this developed into the "Mother and Child" worship

# በልዩ ልዩ አካባቢዎች መጠሪያ ስማቸው

- በጀርመን - ድንግል ሄርታ ልጇን ታቅፋ
- ስካንዲኒቪያ - ዲሳ ከልጇ ጋር
- ግብጽ - አይሲስና ልጇ ኦሲሪስ (ወይም ሆረስ)
- ሕንድ - ዴቫኪና ክሪሽና (እንዲሁም- አይሲና ኢስዋራ)
- በእስያ - ሲይቤሌና ዲኦኢዩስ
- ሮም - ፍርቱናና ጁፒተር-ፑኤር (ሕጻኑ ጁፒተር)፤
- ሮም - ማዶናና ልጇ
- ግሪክ - ሴረስና ልጇን ታቅፋ (አይሪንና ፐሉተስ)
- ቲቤት፣ ቻይናና ጃፓን -- ሺንግ  ማኡ ልጇን ታቅፋ
- በኤፌሶን - ዲያና (የፍሬያማነት እናት)
- ብሪታኒያ - ቪርጎ ፓቲቱራ (የአምላክ እናት)

# ሳሚራሚስና ልጇ ታሙዝ







# ሳሚራሚስና ታሙዝ …

- በሓውልቶቹና በስዕላቱ መካከል ያለውን አንድነት አስተውሉ






# የሳሚራሚስ ልዩ ስሞች (ግሪክ/ሮም/ አማርኛ)

- የሰማይ ንግስት
- ሄስቲያና ቬስታ - የመለኮት ማደሪያ
- አፍሮዳይት/ ቬነስ - የፍቅር አምላክ
- አርትሚስ/ ዲደና - የአደንና የልጅ መውለድ አምላክ
- አቴና/ ሚንረቫ - የእደጥበብ፣ ሰለፍና ጥበብ አምላክ
- ዲምተር/ ሴረስ - የሚያድጉ ነገሮች አምላክ
- ጋኤ/ ቴራ - የፍሬያማ ምድር ምሳሌ
- ሄራ/ ጁኖ - የትዳርና የሴቶች ጠባቂ
- ሄስቲያ/ ቭሰታ - የእሳት ስፍራ አምላክ






DER GÖTZE MOLOCH.
Wie Ihme die Kinder zum Opfer in seine
glüende Arme gegeben.



# ሳሚራሚስ/አሽታሮት

- የፀሐይ ብርሃን እንደ አክሊል








# በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

- በእስራኤል ሕዝብ መካከል የአሕዛብ አማልክት

    -የባቢሎን፣ የግሪክና የግብጽ አማልክት አምልኮ



# ተሙዝና የፀሐይ አምላክ

- 1. **መጽሐፈ መሳፍንት**
- በአልና አሽታሮት

- **2. ሕዝቅኤል ያየው ራዕይ**
- የእስራኤል ቤት ጣዖታት ሥዕል
- ታሙዝ
- ፀሐይ

- **3. በትንቢተ ኤርሚያስ**
- የሰማይ ንግሥት
- ስዕለት
- ምስልዋን ማበጀት
- ቁርባንን ማቅረብ

# 1. በአል(ኒምሩድ)ና አሽታሮት(ሳሚራሚስ)

- መሳ.2:10፤ ትውልድ ሁሉ ደግሞ ወደ አባቶቻቸው ተከማቹ፤ ከእነዚያም በኋላ እግዚአብሔርን ለእስራኤልም ያደረገውን ሥራ ያላወቀ ሌላ ትውልድ ተነሣ። 11 የእስራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነ ነገር አደረጉ፥ በኣሊምንም አመለኩ። 12 ከግብፅ ምድርም ያወጣቸውን የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ተዉ፥ በዙሪያቸውም ካሉት ከአሕዛብ አማልክት ሌሎችን አማልክት ተከተሉ፥ ሰገዱላቸውም፤ እግዚአብሔርንም አስቈጡ። 13 እግዚአብሔርንም ትተው በኣልንና አስታሮትን አመለኩ።

# 2. ትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕ. 8

- ሕዝ.8:3፤ እጅ መሳይንም ዘረጋ በራስ ጠጕሬም ያዘኝ፤ **መንፈስም በምድርና በሰማይ መካከል አነሣኝ፥ በእግዚአብሔርም ራእይ** ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ሰሜን ወደሚመለከተው ወደ ውስጠኛው አደባባይ በር መግቢያ አመጣኝ፤ **በዚያም ቅንዓት የሚያነሣሣ የቅንዓት ጣዖት ተተክሎ ነበር**።
- ሕዝ.8:10፤ እኔም ገባሁና እነሆ፥ በግንቡ ዙሪያ ላይ የተንቀሳቃሾችና የርኩሳን አራዊት ምሳሌ **የእስራኤልንም ቤት ጣዖታት ሁሉ ተስለው አየሁ**። 11 በፊታቸውም ከእስራኤል ቤት ሽማግሌዎች ሰባ ሰዎች ቆመው ነበር፥ በመካከላቸውም የሳፋን ልጅ ያእዛንያ ቆሞ ነበር፥ ሰውም ሁሉ እያንዳንዱ በእጁ ጥናውን ይዞ ነበር፥ የዕጣኑም ጢስ ሽቱ ይወጣ ነበር። 12 እርሱም። የሰው ልጅ ሆይ፥ የእስራኤል ቤት ሽማግሌዎች በጨለማ እያንዳንዱ በስዕሉ ቤት የሚያደርጉትን አይተሃልን? እነርሱ። እግዚአብሔር አያየንም፤ እግዚአብሔር ምድሪቱን ትቶአታል ይላሉና አለኝ።

# ተሙዝና የፀሐይ አምልኮ


- ሕዝ.8:13፤ እርሱም። ደግሞ ተመልሰህ ከዚህ የበለጠውን የሚያደርጉትን ታላቅ ርኵሰት ታያለህ አለኝ። 14 **ወደ ሰሜንም ወደሚመለከተው** ወደ እግዚአብሔር ቤት በር መግቢያ አመጣኝ፤ እነሆም፥ **ሴቶች ለተሙዝ እያለቀሱ በዚያ ተቀምጠው ነበር።** 15 እርሱም። የሰው ልጅ ሆይ፥ ይህን አይተሃልን? ደግሞ ተመልሰህ ከዚህ የበለጠ ርኵሰት ታያለህ አለኝ።

- ሕዝ.8:16፤ ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ውስጠኛው አደባባይ አመጣኝ፥ እነሆም፥ በእግዚአብሔር መቅደስ መግቢያ ፊት በወለሉና በመሠዊያው መካከል ሀያ አምስት የሚያህሉ ሰዎች ነበሩ ጀርባቸውም ወደ እግዚአብሔር መቅደስ **ፊታቸውም ወደ ምሥራቅ ነበረ፤ እነርሱም ወደ ምሥራቅ ለፀሐይ ይሰግዱ ነበር።**

# የጥንታዊያን የፀሐይ አምልኮና ምልክቶች








# በካቶሊክ







# በኢትዮጲያ







# 3.ትንቢተ ኤርሚያስ

## ሳሚራሚስ - የሰማይ ንግስት

- ኤር.7:17-19 እነርሱስ በይሁዳ ከተሞች ውስጥና በኢየሩሳሌም አደባባይ ላይ የሚያደርጉትን አታይምን? 18 ያስቈጡኝ ዘንድ፥ **ለሰማይ ንግሥት እንጐቻ እንዲያደርጉ ለሌሎችም አማልክት የመጠጥ ቍርባን እንዲያፈስሱ** ልጆች እንጨት ይሰበስባሉ፥ አባቶችም እሳት ያነድዳሉ፥ ሴቶችም ዱቄት ይለውሳሉ። 19 እኔን ያስቈጣሉን? ይላል እግዚአብሔር፤ ለፊታቸውስ እፍረት አይደለምን?

# የሰማይ ንግስት …

- ኤር.44:15 ሚስቶቻቸውም **ለሌሎች አማልክት ማጠናቸውን** ያወቁ ሰዎች ሁሉ በዚያም የቆሙ ሴቶች ሁሉ፥ በግብጽ ምድር በጳትሮስ የተቀመጡ ሕዝብ ሁሉ፥ ታላቅ ጉባኤ ሆነው ለኤርምያስ መለሱለት እንዲህም አሉ። 16 አንተ በእግዚአብሔር ስም የነገርኸንን ቃል አንሰማህም።
- 17 ነገር ግን እኛና አባቶቻችን ነገሥታቶቻችንም አለቆቻችንም በይሁዳ ከተሞች በኢየሩሳሌም አደባባይ እናደርገው እንደ ነበረ፥ **ለሰማይ ንግሥት እናጥን ዘንድ የመጠጥንም ቁርባን እናፈስስላት ዘንድ ከአፋችን የወጣውን ቃል ሁሉ በእርግጥ እናደርጋለን**፤ በዚያን ጊዜም እንጀራ እንጠግብ ነበር፥ መልካምም ይሆንልን ክፉም አናይም ነበር።
- 18 ለሰማይ ንግሥት ማጠንን ለእርስዋም የመጠጥን ቍርባን ማፍሰስን ከተውን ወዲህ ግን፥ እኛ በሁሉ ነገር ተቸግረናል፥ በሰይፍና በራብ አልቀናል። 19 እኛስ ለሰማይ ንግሥት ባጠንንላት የመጠጥንም ቍርባን ባፈሰስንላት ጊዜ፥ በውኑ ያለ ባሎቻችን ምስልዋን ለማበጀት እንጐቻ አድርገንላት ኖሮአልን? የመጠጥንም ቍርባን አፍስሰንላት ኖሮአልን?

# እውቀት

- ሆሴ.4:6፤ **ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል**፤ አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ፤ የ**አምላክህንም ሕግ ረስተሃልና** እኔ ደግሞ ልጆችህን እረሳለሁ።

- ኤር.50:6 **ሕዝቤ የጠፉ በጎች ሆነዋል፤ እረኞቻቸው አሳቱአቸው**፥ በተራሮችም ላይ የተቅበዘበዙ አደረጉአቸው፤ ከተራራ ወደ ኮረብታ አለፉ፥ በረታቸውንም ረሱ።

- ዘካ.11:5፤ የገዙአቸው ያርዱአቸዋል፥ ራሳቸውንም እንደ በደለኞች አድርገው አይቈጥሩም፤ የሸጡአቸውም። ባለ ጠጋ ሆነናልና እግዚአብሔር ይመስገን ይላሉ፤ **እረኞቻቸውም አይራሩላቸውም**።

# እውነት

- ዮሐ.8:31-32 ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ። እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ **32 እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል** አላቸው።
- ዮሐ.8:35-36 ባርያም ለዘላለም በቤት አይኖርም፤ ልጁ ለዘላለም ይኖራል። 36 እንግዲህ **ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ።**
- ዮሐ.14:6-7 ኢየሱስም። **እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም**። እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር። ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ አይታችሁትማል አለው።

# ጥበብ

- ዮሐ.10:8-12 ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው፤ ዳሩ ግን በጎቹ አልሰሙአቸውም። 9 በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል። 10 ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ **እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ**። 11 መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል። 12 እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኲላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኲላም ይነጥቃቸዋል በጎቹንም ይበትናቸዋል።

- ማቴ. 24:4 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። 5 ብዙዎች፦ እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ።

- 1ዮሐ.2:18 ልጆች ሆይ፥ መጨረሻው ሰዓት ነው፥ የክርስቶስም ተቃዋሚ ይመጣ ዘንድ እንደ ሰማችሁ አሁን እንኳ ብዙዎች የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ተነሥተዋል፤ ስለዚህም መጨረሻው ሰዓት እንደ ሆነ እናውቃለን።

# የአብን ፈቃድ

- ዘዳ.18፡15-19፤ አምላክህን እግዚአብሔርን በኮሬብ ስብሰባ ተደርጎ በነበረበት ቀን። እንዳልሞት የአምላኬን የእግዚአብሔርን ድምፅ ደግሞ አልስማ፥ ይህችን ታላቅ እሳት ደግሞ አልይ ብለህ እንደ ለመንኸው ሁሉ፥ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፤ እርሱንም ታደምጣለህ። 17 እግዚአብሔርም አለኝ። የተናገሩት መልካም ነው፤ 18 ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፤ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፥ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፤ 19 በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀለለታለሁ።

- ዮሐ.5:30 እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፥ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና።

- ዮሐ.5:43 እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ አልተቀበላችሁኝምም፤ ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ እርሱን ትቀበሉታላችሁ። 44 እናንተ **እርስ በርሳችሁ ክብር የምትቀባበሉ ከአንዱም ከእግዚአብሔር ያለውን ክብር የማትፈልጉ፥ እንዴት ልታምኑ ትችላላችሁ**? 45 እኔ በአብ ዘንድ የምከሳችሁ አይምሰላችሁ፤ የሚከሳችሁ አለ፤ እርሱም ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው። 46 **ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር፤ እርሱ ስለ እኔ ጽፎአልና። 47 መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ**?

- ቆላ.2:2-4 ልባቸው እንዲጸናና፥ በፍቅርም ተባብረው በማስተዋል ወደሚገኝበት ወደ መረዳት ባለ ጠግነት ሁሉ እንዲደርሱ የእግዚአብሔርንም ምሥጢር እርሱንም ክርስቶስን እንዲያውቁ እጋደላለሁ። 3 የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነውና። 4 ማንም በሚያባብል ቃል እንዳያስታችሁ ይህን እላለሁ።

- ዮሐ.17:1-2 ኢየሱስም ይህን ተናግሮ ወደ ሰማይ ዓይኖቹን አነሣና እንዲህ አለ። አባት ሆይ፥ ሰዓቱ ደርሶአል፤ ልጅህ ያከብርህ ዘንድ፥ በሥጋም ሁሉ ላይ ሥልጣን እንደ ሰጠኸው፥ ለሰጠኸው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸው ዘንድ ልጅህን አክብረው። 3 እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላከኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።

- ዳን.12:4፤ ዳንኤል ሆይ፥ አንተ ግን እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ ቃሉን ዝጋ፥ መጽሐፉንም አትም፤ ብዙ ሰዎች ይመረምራሉ፥ እውቀትም ይበዛል።
-

# ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል

- ሕዝ.13:19፤ ***ውሸታችሁን ለሚሰሙት ሕዝቤ እየዋሻችሁ*** ሞት የማይገባቸውን ነፍሳት ትገድሉ ዘንድ በሕይወትም መኖር የማይገባቸውን ነፍሳት በሕይወት ታኖሩ ዘንድ ስለ ጭብጥ ገብስና ስለ ቍራሽ እንጀራ ***በሕዝቤ ዘንድ አርክሳችሁኛል***።
- 20 ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። እነሆ፥ ***እኔ ነፍሳትን እንደ ወፍ በምታጠምዱባት በመከዳችሁ ላይ ነኝ***፥ ከክንዳችሁም ወስጄ እቀድዳታለሁ፥ እንደ ወፍም የምታጠምዱአቸውን ነፍሳት እለቅቃለሁ።
- 21 ሽፋኖቻችሁን ደግሞ እቀድዳለሁ ሕዝቤንም ከእጃችሁ አድናለሁ፥ ከዚያም ወዲያ በእጃችሁ ለመታደን አይሆኑም፤ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ።
- 22፤ እኔም ያላሳዘንሁትን የጻድቁን ልብ በውሸት አሳዝናችኋልና፥ ***በሕይወትም ይኖር ዘንድ ከክፉ መንገድ እንዳይመለስ የኃጢአተኛውን እጅ አበርትታችኋልና***
- 23 ስለዚህ ከንቱን ራእይ እንግዲህ አታዩም ምዋርትንም አታምዋርቱም፥ ***ሕዝቤንም ከእጃችሁ አድናለሁ፤ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ***።